የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ
ውጭ ጉዳይ ቢሮ

Berghof Foundation

# የአገራዊ ምክክር የባለሙያዎች መመሪያ መፅሐፍ

## ዋና ማጠቃለያ

## መነሻ

ባለፉት አስርት አመታት፣ አገራዊ ምክክሮች የአመጽ መስፋፋትን ለማሰወገድ፤ የፖለቲካ ቀውስን እና ሽግግሮችን ለመግራት እንደ ዋነኛ መሳሪያ መታየት ጀምረዋል። ምንም እንኳን በመንግስታት፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሲቪል ማህበራት እና ታጣቂ ኃይሎች፤ እንዲሁም በአለም-አቀፍ ፖሊሲ፤ ሙያዊ፤ ዲፕሎማሲያዊ እና ለጋሽ ክበቦች መካከል በስፋት ውይይት የሚደረግባቸው ቢሆንም፣ የእውቅናቸውን ያህል እስካሁን ድረስ የፅንሰ-ሃሳብ ግልፅነት ይጎድላቸዋል። በተጨማሪም አገራዊ ምክክርን ከፖለቲካ አጣብቂኝ፤ ከሚከፋፍሉ የግጭት ክስተቶች እና ከምስቅልቅል የሽግግር ወቅቶች ለመሻገሪያነት እንደ አማራጭ መፍትሄ ለመጠቀም ለሚሹ  አካላትም ቢሆን ጥልቅ ሙያዊ እውቀት የሚሠጡ፤ እንደ የተግባር መመሪያ እና ግብአት የሚያገለግሉ ውስን ጽሑፎች ብቻ ይገኛሉ፡፡

ይህ የመመሪያ መፅሃፍ ቀደም ሲል በተካሄዱ ተከታታይ የትግበራ ጥናቶች ላይ በመመስረት የተዘጋጀ በመሆኑ፤ በአገራዊ ምክክር ዙሪያ በሳል ክርክሮች እንዲካሄድ ለማገዝ፤ የተለያዩ አካባቢዎችን ምልከታዎችንና ተሞክሮዎችን በማጣመር ለማቅረብ ያለመ ነው። የመመሪያ መፅሃፉ ሁለት ዓላማዎችም፤ (1) የሀገራዊ ምክክሮች ጽንሰ-ሃሳባዊ ትንታኔ ለማቅረብ እና (2) የምክክር ሂደቶች ለሚያመቻቹ አካላት እንደ የትግበራ ማንዋል እንዲያገልገል ታስቦ ነው፡፡ በተጨማሪም የውጫዊ ተዋናዮች ሚናን እና አገራዊ የምክክር ሂደቶችን እንዴት በአግባቡ ሊደግፉ እንደሚችሉ ይዳስሳል፤ ነገር ግን በዋነኛነት የአገራዊ ምክክር ሂደቶችን በግንባር ቀደምትነት ለሚመሩ ውስጣዊ አካላት በሂደቱ ቀረፃ፤ አካሄድና ትግበራ ወቅት በሚደርሱባቸው ውሳኔዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

## ፅንሰ-ሃሳቡ

አገራዊ ምክክሮች በሃገራቱ ባለቤትነት የሚካሄዱ ፖለቲካዊ ሂደቶች ሲሆኑ፤ በሰፊው ብሄራዊ ባለድርሻ አካላት መካከል እጅግ ፈታኝ ፖለቲካዊ ቀውሶችን፣ የድህረ--ጦርነት ሁኔታዎችን ወይም ዘላቂ ፖለቲካዊ ሽግግሮችን በሚመለከት በሃገር-አቀፍ ደረጃ ብሄራዊ መግባባትን ለመፍጠር ያለሙ ናቸው። አገራዊ ምክክሮች እንደ ሃገራቱ የፖለቲካ አውድ መሰረት፣ ለሚከተሉት መሠረታዊ ጉዳዮች ማስፈፀሚያ ስልቶች ሊያገለግሉ ይችላሉ፤ (ሀ) ***ቀውስን ለመከላከል እና ለመግታት፡-*** የአጭር-ጊዜ ትልም ያለው፣ የትጥቅ አመጽን ለማስቀረትና ለመግታት፤ የፖለቲካ አጣብቂኝን ለመፍታት እና በትንሹ ፖለቲካዊ መግባባትን ዳግም ለመፍጠር (ለምሳሌ፤ ቱኒዚያ)፤ ወይም (ለ) ***ለሰርነቀል ለውጦች፡- ከረጅም-ጊዜ አቅጣጫ***፣ የመንግስትንና የህዘቦችን ግንኙነቶች መልሶ ለማስታረቅ፤  ወይም ተቋማዊ እና ህገ-መንግስታዊ ለውጦችን በመተግበር አዲስ ማህበረሰባዊ ስምምነትን ለመመስረት እንደ ስልት የሚያግዝ ነው (ለምሳሌ፤ የመን)።

አገራዊ ምክክሮች ፖለቲካዊ ቀውሶችን እና የትጥቅ አመጽን ለማስወገድ እና የለውጥ ሂደቶችን ለማሳለጥ እንደ አንድ ስልት ሆነው የሚያገለግሉ ሲሆን፤ ከሌሎች እንደ ሽምግልና እና ድርድር ከመሳሰሉት ስርነቀል የግጭት አፈታት ዘዴዎች ጋር በጣምራ የሚካሄዱ ናቸው፡፡ አገራዊ ምክክሮች በግልጽ ከሚለዩበት ባህሪያት መካከል የአጠቃላይ ሂደቱ አመላካችነት (ከውጤቱ ይልቅ)፣ የላቀ የተሳትፎ አድማስና ደረጃው (የተለያዩ የማህበረሰቡን ክፍሎች የሚያገናኝ መሆኑ) እንዲሁም በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚደራጅና የሚከናወን መሆኑ (የውጫዊ ተዋናያን ሚናን ድጋፍ በመስጠት የተገደበ በማድረግ) ናቸው። ይሁንና በተግባርም እንደሚስተዋለው፣ ማንኛውም ዘላቂ መፍትሄ ለማስገኘት የአውድ-ተኮር ስልቶች እና ሂደቶችን ጥምረት የሚጠይቅ መሆኑ ነው። አገራዊ የምክክር ሂደት በሽምግልና በሚካሄድ የዝግጅት ምዕራፍ እንዲሁም ወሳኝ የፖለቲካ ክስተቶችን በጥልቅ ፖለቲካዊ ድርድሮች በመፍታት ሂደት ውስጥ ሊያልፍ ይችላል። በተጨማሪ፣ አገራዊ ምክክሩ ከድርድር ወይም ከሽምግልና ሂደቱ አስቀድሞ፣ በኋላ ወይም በተጓዳኝ ሊካሄድ ይችላል።



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA

swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

# ከፅንሰ-ሃሳብ እስከ ትግበራ፤ የሂደት ንድፍ አማራጮች እና ተግባራዊ ታሳቢዎች

እያንዳንዱ አገራዊ ምክክር እጅግ አውድ-ተኮር ከሆኑ ፍላጎቶች እና ከሂደቱ አላማ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ የራሱን አወቃቀር ያጎለብታል። ይሁንና ቁልፍ ተግባሮችን ከማስፈጸም አኳያ በአገራዊ ምክክሮች መካከል የአወቃቀር ተመሳሳይነት ማየት ይቻላል፤ (በገጽ.5 የቀረበውን አገራዊ ምክክር ማዕቀፍ ይመልከቱ)። የተሻለ ግልፅነትን ለመፍጠር እንዲቻል የመመሪያ መፅሐፉ በተለያዩ ምዕራፎች (የዝግጅት፣ የሂደት እና የትግበራ) መካከል ልዩነቶቻቸውን ከማመላከት ባሻገር የሚኖሯቸውን ተዛማጅ ተቋማትን በግልፅ ያስቀምጣል። ይሁንና በተግባር እንደሚታየው፣ ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላኛው የሚደረገው ሽግግር አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ ያልሆነ፤ በተደጋጋሚ የሚቆራረጥበት እና የሚከለስበት ሁኔታ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡

## የዝግጅት ምዕራፍ

የዝግጅት ምዕራፍ በአብዛኛው በውስጡ መለስተኛ የድርድር ሂደትን ያካትታል። ይህ ወቅት ለሂደቱ ጠቃሚ በሚሆነው ማዕቀፍ ላይ ለመደራደር፤ እንዲሁም የተከሰተውን ግጭት በሰላማዊ፣ ፖለቲካዊ እና በምክክር-መር አካሄድ ለመፍታት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በሚሰጡ ተዋናዮች መካከል የተሻለ ግንኙነትን ለመፍጠር ያስችላል። ምንም አንኳን የፖለቲካ ድርድር የሚካሄድ ቢሆንም፤ ከዚህ ምዕራፍ ጋር የሚዛመዱ ቴክኒካዊ ጉዳዮችም እጅግ ወሳኝና ለቀጣዩ ሂደት አንድምታ ያላቸው ናቸው፡፡ የአገራዊ ምክክሩ መጀመር ይፋ ከመደረጉ በፊት የዝግጅት ሂደቱ ሊቀረጽና ስምምነት ሊደረስበት እና አብዛኛውን ጊዜ ራሱን የቻለ ሁሉን-አቀፍ ተቋሟዊ ማዕቀፍ ሊዘጋጅለት ይገባዋል።

በዚህ ምዕራፍ የሚካተቱ ቁልፍ ተግባራት (1) የሂደቱን ዓላማ፤ ግቦች፣ እና ወሰን ግልፅ የሚያደርግ ስልጣን/ኃላፊነትን መደንገግ፤ (2) ሂደቱን እና ተሳታፊዎችን ማዘጋጀት፤ እና (3) በራስ-መተማመንን መገንባት ናቸው። የዝግጅቱ ቅርፅ ምርጫም አብዛኛውን ጊዜ በሂደቱ ዓላማ፤ በሚኖሩት ሃብቶች፤ እና በዋነኛ ባለድርሻ አካላት ፍላጎቶች የሚወሰን ነው። በሃሳብ ደረጃ፤ በአገራዊ ምክክሩ ማዕከላዊ ዓላማ እና ቁልፍ መርሆዎች ላይ የጋራ መግባባት ላይ የሚያደርስ አካሄድ መከተል ይገባል።

## ቁልፍ ታሳቢዎች

- **ግልፅ መሆን፡** ሀገራዊ ምክክሮች በተጨባጭ ምንን እንደሚያሳኩ፤ እነዚህንም በሰፊው የሽግግር ሂደቶቹ በግልፅ በማካተት ማስረጽ፤
- **ባለቤትነት፡** ዋነኛ ባለድርሻ አካላትን በቅንነት ማቅረብ፣ ሰፋፊ ምክክሮች ማካሄድ እና አካታች የዝግጅት ስርዓት መኖር፤ ባለቤትነትና ህጋዊነትን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ ብሄራዊ ተዋናዮች በአገራዊ ምክክር ሂደት ንድፍና ትግበራ ወቅት ግንባር ቀደም ሚና ሊኖራቸው ይገባል።
- **አካታችነት፡** የዝግጅት ምዕራፉ የበርካታ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ከግምት ውስጥ የሚያገባ አካታች አካሄድን መከተል አለበት። ከዋነኛ ተዋናዮች መካከል (መንግስት) በዝግጅቱ ተቋማት ላይ ስልጣኑን በማሳረፍ እና አጠቃላይ ሂደቱን በመጥለፍ አደጋ ሊፈጥር ይችላል።
- **ግልፅ ስልጣን እና አላማ፡** ሂደቱ ምን እንዲያሳካ እንደሚጠበቅ (ምን እንደማያሳካ) ግልፅ መሆን አስፈላጊ ነው። ይህም የሂደቱን ንድፍ አግባብነት ለማመላከት እና ከልክ ያለፈ ተስፋን ለመግራት ያግዛል።
- **ሊቀመንበርነት፡** ለዝግጅት ምዕራፍ ትክክለኛውን ሊቀመንበር መምረጥ መቻል የሂደቱን እቅድ ተአማኒነት ለማመላከት ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ቅቡልነትን ያስገኛል።
- **ፈጥኖ ለመድረስ በዝግታ መጓዝ:** የዝግጅት ምዕራፉ የአጠቃላይ ሂደቱ መንደርደሪያ ቢሆንም፤ እንደ ቀጣይ ምዕራፎች በተመሳሳይ ጥንቃቄ እና የትኩረት ደረጃ መታቀድ እና መተግበር አለበት።
- **ተቋማት እና የአሰራር ስርዓቶች፡** የሂደቱን ተግባራት፣ ስልጣን፣ ሊቀመንበር እና የውሳኔ-አሰጣጥ ስርዓት በግልፅ መጠቆም አለባቸው። የአዘጋጁ አካል ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት እንዲችል፤ የሂደቱ ተሳታፊዎች የመምረጫ መስፈርትን፤ አጀንዳ የመወሰኛ አማራጮችን፤ እና በሂደቱ ወቅት ለሚያጋጥሙ አጣብቂኝ ጉዳዮች አማራጭ መፍትሄዎቸን የማዘጋጀት የሥራ ድርሻዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡
- **መተማመን የሚገነቡ እርምጃዎች አስፈላጊነት፡** ይህ ምዕራፍ በአብዛኛው በውስብስብ ድርድሮች የሚገለጽ ቢሆንም፤ መተማመንን በሚገነቡ እርምጃዎች ከተደገፈ ግንኙነትን እና አመኔታን ለማጎልበት የተለየ እድሎችን ይፈጥራል።



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra
Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA
swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

- **ሐብቶች**፡ አገራዊ ምክክሮች እጅግ ከፍተኛ የፋይናንስ እና የሰው ሃብቶች ይጠይቃሉ። ስለሆነም የዋና ዋና ለጋሽ ሃገራት እና አለም-አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ድጋፎችን ማስገኘት አስፈላጊ ነው። አስተማማኝ የፈንድ አጠቃቀም ማዕቀፍ (ለምሳሌ፤ የትረስት ፈንድ) ማዘጋጀትም በእኩል ደረጃ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም በሂደቱ ከመንግስት ውጭ የታጠቀ ኃይል የሚሳተፍ ከሆነ ለቡድን (ለአስተዳደር፣ ሎጅስቲክስ ወዘተ…) የሚመደበው ፈንድ ፖለቲካዊ እና ህጋዊ ጥያቄዎችን ስለሚያስነሳ ጥንቃቄና ብስለት የተሞላበት ፖለቲካዊ አካሄድ በመከተል ማስተናገድን ይሻል፡፡

## የሂደት ምዕራፍ

የሂደት ምዕራፍ የአገራዊ ምክክሩ ዋነኛው የህዝብ ምዕራፍ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ ምዕራፍ ጋር የሚዛመዱ ቁልፍ ደረጃዎች፣ ቅደም-ተከተሎች እና ስነስርዓቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

**አጀንዳ የመወሰን**፡ አጀንዳ የመለየቱ ሂደት በግልፀኝነት እና አካታች በሆነ አካሄድ ከተከናወነ የአገራዊ ምክክሩን ባህሪ የበለጠ ግልጽ ያደርጋል፣ ተዋንያን ለሂደቱ ቁርጠኛ እንዲሆኑ ፤ እና መተማመንን ለማጎልበትም ሆነ በአቋሞች እና ራዕይ ላይ የጋራ አረዳድን ለመፍጠር መለማመጃ ሆኖ ያገለግላል።

**እምነት የሚጣልበትና ተቀባይነት ያለው አስተባባሪ ማፈላለግ**፡ የአስተባባሪ ምርጫ አብዛኛውን ጊዜ ከአጠቃላይ ሂደቱ ምን እንደሚጠበቅ አጉልቶ ያመላክታል። እምነት የሚጣልበትና በብዙሃኑ ተቀባይነት ያለው አስተባባሪ መምረጥ የላቀ አቅምን እንዲሁም ውስጣዊ አሸማጋዮችም ይህን ወሳኝ ሚና ለመወጣት ተገቢውን የኃላፊነት ደረጃ ይፈጥላቸዋል፡፡

**የተሳታፊ መጠን መወሰን**፡ ምናባዊ/የሚያግባባ መጠን የለም፤ ይልቁንም ሂደቱ እንዲያሳካ በሚጠበቀው ዓላማ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤ (ቀውስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ወይንስ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት)። የሂደቱ ተሳታፊ መጠን የሚወሰነው የተለያዩ አማራጮችን በማመዛዘን እና ግምታዊ አቀራረቦች በማገናዘብ ድምር ውጤት መሆን አለበት። ይሁንና አካታች የሂደት ንድፍ በሚያስከትለው  አስተዳደራዊ ፍላጎት ከመጠመድ ይልቅ፤ ተሳትፎውን በተለያዩ አግባቦች (በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ፣ ወዘተ) ለማስተናገድ ፈጠራ የታከለበት የሂደት ንድፍ እሳቤ መከተል ይገባል።

**ተሳታፊዎችን መምረጥ**፡ የተሳታፊዎች ምርጫ በአብዛኛው የበርካታ ደረጃዎች አካሄድ መተንተን ስለሚጠይቅ፤ ሂደቱ ከሚያተኩርበት ጉዳይ(ዮቹ) ጋር የሚገናኘው ህብተሰብ ማኅበራዊ ትስስርን በሚያንፀባርቅ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል። የአገራዊ ምክክሮችን ሰፊ መሠረት እና አካታችነት ለማረጋገጥ የተሳታፊዎች ምርጫ አንዱ ቁልፍ መሳሪያ ሲሆን፤ የፓርቲዎች የተሳትፎ ድርሻ በህብረተሰቡ ባላቸው የቅቡልነት ደረጃ መሠረት የሚወሰን እንጂ (ለሁሉም ፓርቲዎች እኩል የመቀመጫ ቁጥር የሚያደላድል ሊሆን አይገባውም)። ህጋዊነቱንም እንዲያመላከት የምርጫ መስፈርቱ እና የአሰራር ዘዴዎቹ ወጥነት፣ ፍትሃዊነት እና ግልፀኝነት ያላቸው (በገሃድ የሚታወቁ) መሆን ይኖርባቸዋል።

**ግልፅ መርሆዎችንና የአፈፃፀም መመሪያዎችን ማስቀመጥ**፡ ፍትሃዊ የአሠራር ስርዓት ህጋዊነትን ለማስገኘት ጠቃሚ ጉዳይ በመሆኑ፤ ሂደቱን የመገምገምም አቅምን እና የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

**የውሳኔ-አሰጣጥ እና የጋራ መግባባት መገንቢያ ስርዓት ማዘጋጀት**፡ የአገራዊ ምክክሮች ውሳኔ-አሰጣጥ በተለምዶ በጋራ መግባባት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፤ ሂደቱን አብዛኛውን ጊዜ አድካሚና አታካች ያደርገዋል፡፡ ብዙዎቹ ሂደቶች የበርካታ ደረጃዎች አቀራረብ በመከተል በውስጣቸው የሚፈቱበትን ስርዓት ያካትታሉ፡፡ በአግባቡ የሚተገበር ከሆነም በብዙሃን ተዋናያኖች ዘንድ ለሂደቱም ሆነ ለውጤቶቹ ህጋዊነትን እና የጠበቀ ቁርጠኝነትን ያስገኛል፡፡

**ህዝብን ማሳተፍ**፡ ሂደቱ በሰፊው ህብረተሰብ የሚካሄድ መሆኑን ለማረጋገጥ ህዝብን ተደራሽ በሚያደርግ እና በመመካከር ማካሄድ አስፈላጊ ነው። ሂደቱን ለመከታተልም ሆነ በተለያዩ ደረጃዎች ግብአቶችን እንዲያቀርብ ማስቻል የህዝብን ድጋፍና ይሁንታ ይጨምራል። የሚቀርቡ ግብአቶችን በሂደቱ ውስጥ መልሶ ትርጉም ባለው መልኩ ለማካተት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋትም እጅግ ጠቃሚ ነው።

**የድጋፍ መዋቅሮች፤ አጣብቂኝ ውስጥ የገቡ ጉዳዮች መፍቻ ስርዓት እና የደህንነት መረቦችን መፍጠር**፡ እነዚህ መዋቅሮች በዋናነት የሚቀረጹት የሚከሰቱ አለመግባባቶችና ውዝግቦችን ለመፍታት እንዲያግዙ፤ እንዲሁም ድርድሩንና የምክክር ሂደቱን ማዕከል ወደሃዲዱ መልሶ ለማስቀጥል እንዲያስችሉ ነው፡፡ በተጨማሪም አገራዊ ተግባቦት መፍጠሪያም ሆነ ቅራኔዎች መፍቻ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን መቀመር አስፈላጊ ነው፡፡


Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra
Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA
swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

## የትግበራ ምዕራፍ

በአገራዊ ምክክሩ የሂደት ምዕራፍ ወቅት የተለያዩ ውጤቶችን ለማስገኘት እድል ይኖራል፡፡ እነዚህም ውጤቶች ***የማይጨበጡ*** (መልካም ግንኙነት የመመስረት፣ የሲቪክ ትምህርት፣ ወዘተ.) እና ***የሚጨበጡ*** (ፖለቲካዊ እና ህገ-መንግስታዊ ለውጦች፣ ወዘተ.) የመሳሰሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ተጨባጭ ውጤቶችን በአግባቡ መተግበር መቻል ውጤቶቹን ለማስገኘት የተኬደበትን ርቀት ያህል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አስቀድሞ ስምምነት በተደረሰባቸው ጉዳዮች ላይ ቅቡልነት እና ቁርጠኝነት በገሃድ የሚገለፀው በዚህ ወቅት ብቻ ነው፡፡ የአገራዊ ምክክሩ ቀዳሚ ውጤቶች በድርድሮችና የሽምግልና ሂደቶች ከሚካሄዱ የተኩስ አቁም ስምምነቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ቢሆኑም፤ ስምምነቱ ላይ የሚደረስበት ሂደት ግን አብዛኛውን ጊዜ የተለየ ሊሆን ይችላል።

አገራዊ ምክክሮች ሂደቶች በግልጽ መርሆዎች ላይ በመመስረት በራስ አነሳሽነት እና አመቻቺነት የሚካሄዱ ሲሆኑ፤ ከሂደቱ መዝጊያ ፕሮግራም በኋላም ቢሆን ቀጣይ እንድምታ አላቸው፡፡ በተጨማሪም በጋራ መግባባት የተቃኘ ሂደት ላይ መሳተፍ በበኩሉ ከፍተኛ ልምድ ያስገኛል፡፡ ከተኩስ አቁም የድርድር ሂደቶች ይልቅ የትግበራ ምዕራፍ በርካታ ህዝብ የሚያሳትፍ መሆኑን ታሳቢ ማድረግ፤ ህዝቡ የሠጣቸው ድጋፎች በትግበራ ምዕራፍ ወቅትም ፍሬ ማፍራት መቀጠላቸውን ማየት ያስችለዋል፡፡ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ የትግበራውን ምዕራፍ ማካሄድ ይቻላል፤ ይህም 1) የትግበራው ማዕቀፍ 2) የዋስትናና የክትትል ስርዓቶች እና 3) የክትትል ምክክር ሸንጎዎችን ያካትታል፡፡ የሂደቱን በጎ መንፈስ በማስቀጠል የትግበራውን ምዕራፍ አካታችና አሳታፊ በሆነ አካሄድ መንደፍ ለትግበራው ጥልቀትም ሆነ የለውጥ ሂደቶችን ለማጠናከር ተጨማሪ ድጋፍ ይሠጣል፡፡

## *ቁልፍ ታሳቢዎች*

- ከአገራዊ ምክክሩ **ከልክ ባለፈ ተስፋ አለመጠበቅ/መቆጠብ ወሳኝ ነው፤** ስለአገራዊ ምክክሩ የሚሠጠው ብይን አጠቃላይ ሂደቱን በማመላከት ጭምር እንጂ ከተጨባጭ ውጤቶች አንፃር ብቻ መሆን የለበትም። በተጨማሪም የአጭር ጊዜ ውጤቶችን ለመተግበር በሚወሰዱ ፈጣን እርምጃዎች ከመርካት/ከመዘናጋት ይልቅ፤ ለሁሉ-አቀፍ የትግበራው ሂደት ጥርጊያውን በማመቻቸት መሠረታዊ ለውጦች ለማሳካት መሆን ይኖርበታል።
- ***ወደ ውጤት የሚያደርሰው*** ሂደት ለውጤቱ ማማር አስፈላጊና ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው፡፡ ከዚህ አንፃር ለአገራዊ ምክክሮች ጠቃሚ የሚሆነው በሁሉም ተዋናዮች አካታችነትና አሳታፊነት **በጋራ መግባባት ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡** ይህም ከጅምሩ ለስምምነቱ ሰፊ ድጋፍን ሊያመቻች እና የትግበራው ስኬታማነት እድልን ይጨምራል፡፡ ሌላኛው ትግበራውን የሚያግዘው ጉዳይ ስምምነቶቹ ከመለስተኛ የጋራ መግባባት አልፈው ተጨባጭ ጥልቅ- ቅራኔዎችንም ለመፍታት ያለሙ መሆናቸው ላይ ነው፡፡
- በአገራዊ ምክክር ሂደቱ የሚካሄዱ የእቅድ እና የዝግጅት ጉዳዮችን መኖራቸው ሳይዘነጋ፤ በተለይም የትግበራው ምዕራፍ በእቅድ የሚገራ ሂደት አለመሆኑን፤ ነገር ግን ለውጥ ተኮር/ስርነቀል ሂደት መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ለትግበራ ግልፅ የሆነ የጊዜ ሰሌዳና የትግበራ ደረጃዎች (ጥብቅ የሆኑ ቀነ ገደቦች የተቀመጠላቸው) መኖር አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን በማንኛውም ጊዜ የሚከለስ ሊሆን ይገባዋል።
- ‘ገንቢ የሆነ አሻሚነት’ አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ሊሆን ቢችልም፤ የትግበራው **ስልቶች እና አካላት በምክረ-ሃሳቦቹ ወይም ስምምነቶቹ** ላይ በ**ግልፅ ቋንቋ** መስፈር ይገባዋል። በተጨማሪም ያልተቋጩ ስምምነቶች ከዳር አስኪደርሱ ድረስ እንዳይዘነጉና እንዳይረሱ የክትትል ስርዓት በማበጀት፤ የሌሎች ስምምነቶች ትግበራንም ጭምር አለማሰናከላቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡
- እንደ እውነታው ከሆነ፣ የአገራዊ ምክክር ትግበራ ምዕራፍ የሂደቱ ማጠናቀቂያ ተደርጎ ‘መወሰድ የለበትም፤ **ይልቁንም በተለያዩ ደረጃዎች ለሚቀጥሉ ተከታታይ ምክክሮች በር የሚከፍቱ** ሊሆን ይገባል፡፡ (ለምሳሌ፣ መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ በምክክሩ ተሳታፊዎች መካከል በሃገር-አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች)፤ ለዘላቂ መዋቅር፤ የሰላም ግንባታ ጽንሰ,ሃሳባዊ ማዕቀፍ (I4P) ከግምት ውስጥ ማስገባት ይበጃል፡፡



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA

swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

# ውጫዊ ተዋናዮች ተሳትፎ

በአገራዊ ባለቤትነትና መሪነት ሲባል አገራዊ ምክክር ሂደቶች ለውጫዊ ዕይታዎች፣ ቅድመ-ሁኔታዎች እና ተዋንያኖች ጫና አይጋለጡም ማለት አይደለም። ውጫዊ/አለም-አቀፋዊ ተዋናዮች በአገራዊ ምክክር ሂደቶች ውስጥ በርካታ ሚናዎችን ይጫወታሉ። እንደ ***አስቻይ***፣ በአለም-አቀፍ ደረጃ ለአገራዊ ምክክሩ ድጋፍን ያጎለብታሉ፣ ተፋላሚ ወገኖችን ለማምጣት ተፅዕኖ ያሳድራሉ፣ ከተቀናቃኝ ወገን ጋር ወደ ምክክር እንዲገቡ ግፊት ያደርጋሉ (ለምሳሌ፣ የጓቲሚላ ቡድን ስምንት)። ይህም የተለያዩ ማበረታቻዎችን (የዕዳ እፎይታ፣ የጋፍ ፓኬጅ) እና ጫናዎችን (የተመጠኑ ማዕቀቦች፤ ገደቦች፣) በማጣመር የሚተገበር ይሆናል። እንደ ***ለጋሽ***፣ አገራዊ የምክክር ሂደቱን ለማካሄድ በቀጥታ የሚሠጥ የፋይናንስ ድጋፍ (የመን) ወይም የፖለቲካ ሂደትን ለሚደግፍ ሃገር በቀል አካል በተዘዋዋሪ በመስጠት (ኔፓል)፡፡ እንደ ***ታዛቢ***፣ በሂደቱ ወቅት ንቁ ሚና ሳይኖራቸው እንደ እማኝ ሆነው በመገኘት፣ ለሂደቱ አለም-አቀፋዊ ድጋፍን በማረጋገጥ፣ በተዋናይ በወገኖች መካከል መተማመን እንዲኖር እንዲሁም ለመቀራረብ እና ለድርድሮች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ይገለፃል። እንደ ***ዋስትና ሰጪ***፣ ለአገራዊ ምክር ሂደቱና ለውጤቶቹ ጥብቅና በመሆን ለትግበራ ቁርጠኝነትን እና ፖለቲካዊ ድጋፋቸውን ይለግሳሉ፡፡ ፓርቲዎቹ ዝቅተኛ መተማመን በሚኖራቸው ሁኔታዎች፣ የውጫዊ ተዋንያን እንደ ታዛቢዎች እና ዋሶች ሆነው ሲሳተፉ በፓርቲዎች መካከል እምነትን ለማጎልበት እና ፓርቲዎቹ በሂደቱ በመሳተፉ ረገድ ቀደም ሲል ያሳደሩት ስጋት ለማስቀረት ሊረዱ ይችላሉ። እነዚህ ሚናዎች ጫናን የማሳረፍ አቅምን የሚጠይቁ በመሆናቸው፣ አብዛኛውን ጊዜ በተፅዕኖ ፈጣሪ መንግስታት፤ አለም-አቀፋዊ እና ክልላዊ ተቋማት የሚሳኩ ናቸው (ለምሳሌ፡ የተባበሩት መንግስታት በጓቲማላ፤ ኳታር እና የአረብ ሊግ በሊባኖስ)።

***እንደ ቴክኒካዊና ሙያዊ ድጋፍ ሰጪ፣*** በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ጭብጣዊ ግብአቶችን በመስጠት (በሂደቱ ንድፍ፣ ስልጣን-ማጋራት፣ ወዘተ.)፣ የክህሎት ስልጠና እና ሙያዊ ተሞክሮዎችን በማካፈል፣ በአገራዊ ምክክር ተሳታፊዎች መካከል ወይም በውጭ ባለሙያዎች እና በተሳታፊዎች መካከል የሚካሄዱ ውይይቶችን በማመቻቸት ያግዛሉ (ለምሳሌ፤ በጆርዳን ዩኤንዲፒ፤ በኔፓል ስዊስ)። እንደ ***አመቻቺ*** በተፈጠሩ ክፍተቶች እንደ ድልድይ ተዋናይ ወገኖችን በማቀራረብ፤ በሂደቱ እምነትን ይገነባሉ ወይም የተወሰኑ ጉዳዮችን ለመፍታት ይረዳሉ፣ በአብዛኛው ተሳታፊዎችን ወደ መደበኛ ያልሆነ መድረክ በጋራ በማምጣት፤ በህጋዊ አካሄድ አዳጋች የሚሆኑ የመፍትሄ አማራጮችን እንዲያፈላለጉ እድል በመስጠት ይሆናል (ለምሳሌ፤ በሊቢያ የተመድ፤ በሱዳን አፍሪካ ሕብረት)። በስተመጨረሻ ቀለል ተደርጎ ሊታይ የማይገባው እንደ ***አስፈፃሚ***፣ ***ተቆጣጣሪ*** እና ***አፅዳቂ***፣ ከአገራዊ ምክክሩ የመነጩ ውጤቶችን ወደ ተግባር ለማሸጋገር ወይም በበላይነት ለመከታተል በኃላፊነት ዕገዛ ያደርጋሉ። ይህ ተግባር ብዙውን ጊዜ በክልላዊ ወይም አለምአቀፋዊ ድርጅቶች ይከናወናል (በየመን የአለም ባንክ፤ በኬንያ የአፍሪካ ታዋቂ ግለሰቦች መማክርት ፓናል)፤ ነገር ግን በአብዛኛው የሃገር ውስጥ ሲቪል ማኅበራት ተቆጣጣሪ ድርጅቶች ጋር ኔትወርኮች ጋር በመደጋገፍ ይካሄዳል፣ ይህም የነባራዊ አውዱ አካል ስለሆኑና በርቀት ወደሚገኙ አከባቢዎች መድረስ ስለሚችሉ ነው፡፡ በውጫዊ ተዋናዩ ባህሪ ላይ በመመስረት፣ ፖለቲካዊ እና ልማታዊ ተዋናይ እንደመሆኑ፣ በአገራዊ ምክክር ሂደት በየምዕራፉ የሚያከናውናቸው የተወሰኑ ተግባራት ይለያሉ፡፡

| | **የፖለቲካ ተዋንያኖች** | **የልማት ተዋንያኖች** |
|---|---|---|
| ዝግጅት | • ማበረታቻዎችን ማስቀመጥ እና ፖለቲካዊ ድጋፍን ማጎልበት፤<br>• ተፅዕኖ ፈጣሪ  አለም-አቀፋዊ እና ክልላዊ ባለድርሻ አካላትን በመድረስ ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤<br>• መተማመንን እና መቀራረብን ለማጎልበት መደገፍ፤ | • ከፈንድ ማዕቀፍ/ገደብ የተቆራኙ ማበረታቻዎችን ማስቀመጥ፤<br>• በሂደቱ የልማት አጀንዳ እንዲካተት የሚወተውቱ ቡድኖችን አቅም መገንባት፤<br>• መተማመንን እና መቀራረብን ለማጎልበት መደገፍ፤<br>• በታችኛው እርከን የሚካሄዱ የህዝብ መረጃ ዘመቻዎችን መደገፍ |
| ሂደት | • ለጭብጣዊ ጉዳዮች እና ለሂደቱ ሙያዊ ድጋፍ ማስጠት፤<br>• እንደ ታዛቢ ወይም ዋስትና ሰጪ በመሆን እምነት የሚጣልበት ሁኔታን መፍጠር፤<br>• አለም-አቀፋዊ ድጋፍን ማረጋገጥ፤<br>• የጎንዮሽ ስብሰባዎችን ማመቻቸት፤ | • የፈንድ ማዕቀፎች፤<br>• ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፣ ለምሳሌ፡- በልማት ጉዳዮች ላይ ለሚያተኩሩ የትግበራ ቡድኖች፤<br>• ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን ማቅረብ፤ ተዛማጅ የስጋት ትንተናዎችን ማካሄድ፤ |


Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra
Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA
swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

| ትግበራ | <ul><li>የውጤቶች ትግበራ መከታተል/መቆጣጠር፤</li><li>ለውጤቶች ትግበራ ድጋፍ አለም-አቀፋዊ ትኩረትን ማስጠበቅ፤</li><li>በውጤቶቹ መሠረት ዘላቂ ተቋማት ለማደራጀት መደገፍ፤</li></ul> | <ul><li>ለውጤቶች ትግበራ የገንዘብ ድጋፍን በማቅረብ ለሰላም አማራጭ ዋስትና መስጠት፤</li><li>ውጤቶችን ለመተግበር ቴክኒካዊ ድጋፍ ማቅረብ፤</li><li>የድህረ-ግጭት ፍላጎቶች ትንተና ማካሄድ፤</li></ul> |
|---|---|---|

## ቁልፍ ታሳቢዎች

- ውጫዊ ተዋናዮች በሚኖራቸው ሚና ላይ አገራዊ ባለድርሻ አካላት እንዲወስኑ መፍቀድ።
- የአገራዊ ባለድርሻ አካላት ሥራዎችን በጥብቅ ትብብር እና ተመጋጋቢነት ማካሄድ።
- ሁሉንም አገራዊ ተዋንያን ከወገንተኛነት በፀዳ መልኩ ማሳተፍ፣ ለምሳሌ እገዳ የተጣለባቸው ቡድኖችን በሚመለከት።
- ለአካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎችእና እሴቶች ተገቢውን ክብርን መስጠት፤ ምንም እንኳን ከአገራዊና አለምአቀፋዊ ሁኔታዎችና እሴቶች ጋር በእኩል ደረጃ የማይዛመዱበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም፤
- የአገራዊ ባለድርሻ አካላት እይታ አመኔታን ከሚያሳጡ የምክክር ሂደቱን ከሚሸረሽሩ ድብቅ ፍላጎቶች መታቀብ፤
- አማራጭ የፈንድ ማሰባሰብ አካሄድን መከተል፤ የሽግግር ምዕራፎች በአብዛኛው የረጅም-ጊዜ ማግባባትን እንደሚጠይቁ እና አፈፃፀሙም ወጥነት ላይኖረው እንደሚችል መገንዘብ፤
- የፈንድ ማሠባሠብ ውሳኔዎችን አገራዊ ባለድርሻ አካላትን በማማከርና በማሳተፍ ማካሄድ፣ እንዲሁም በማኅበረሰቡ ዕይታ አገራዊ ምክክሩ ከልክ በላይ በለጋሾች ድጋፍ ላይ ጥገኛ አለመሆኑን ማረጋገጥ፤
- የወዳጆች እና የድጋፍ ቡድኖች የመሳሰሉ በመመስረት ጥቅም ላይ ማዋል፤ በሰላም ሂደቶች በሚሳተፉ በርካታ ባለድርሻ አካላት መካከል በተለምዶ የሚያጋጥሙ የቅንጅት ተግዳሮቶችን ማስወገድ።
- ስትራቴጂካዊ ቅደምተከተሎች ጋር በሚዛመዱ እና ተሳትፎዎችን ከብሄራዊ ፍላጎቶችን ጋር በሚያስተሳስሩ ስልቶች አገራዊ ምክክሮችን መቃኘት፤ ፍላጎት-ተኮር በሆነና ገለልተኛ አካሄድ የሚከተል እንዲሆን (አቅርቦት ተኮርና በሌላ ወገን የሚጫን/የሚወሰን አካሄድ ይልቅ)፤

# የስኬታማ አገራዊ ምክክር መለኪያዎች

**ቅድመ-ሁኔታዎች፡** ከሌላኛው ወገን ጋር ለመደራደር እና ለመቀራረብ ያለ ዝግጁነት፤ ይህንም በጽኑ እምነት የመፈፀም፤ ለሂደቱ ስኬት ፖለቲካዊ ፍላጎት እና ቁርጥኝነት መኖር፤ ቢያንስ አብሮ ለመስራት መተማመን፤ የአገራዊ ምክክሩን ውስብስብነት እና የስኬት እድል በእውነታው ላይ በመመስረት በመመዘን/በመገምገም ከልክ ካለፉ ተስፋዎች፤ ቁጭት እና የምክክር መሰላቸት መቆጠብ፤ እና የሲቪል ማህበረሰብ ተዋንያን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ትኩረት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲሁም መደበኛ ያልሆኑ እና ባህላዊ ተሰሚነት ያላቸውን አካላትን ማካተት፤

**አለም-አቀፍ/ክልላዊ ተዋናያን፡** የአገራዊ ምክክሩን ጥረት ለመደገፍ እግባብነት ባላቸው አለም-አቀፋዊ እና ክልላዊ ተዋናያን መካከል ቢያንስ እንኳን ፖለቲካዊ መግባባትን መፍጠር፤ ይህንንም በጊዚያዊ ምክክሮች ወይም ተቋሚያዊ በሆነ (የግንኙነት ቡድኖች፣ የወዳጅነት ቡድኖች፣ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክር ቤት አገራዊ ምክክሩን በመጥቀስ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች) አካሄድ መፈፀም፤

**ተገዳዳሪ አስተሳሰብ ያላቸው ቡድኖች፡** ለተደራሽነት አዳጋች የሆኑ የታጠቁ ኃይሎች በቀጣይ የምክክር ሂደቱን እንዳያደናቅፉ ከወዲሁ ለማቀራረብ የሚያስችል ግልፅ ስትራቴጂ መንደፍ፤ ይህም ታጣቂ እና እገዳ የተጣለባቸውን ቡድኖችን ያካትታል።

**አስተባባሪ፡** በሚታወቅ መስፈረት የሚመረጥ፤ በሁሉም ተዋናይ ወገኖች ቅቡልነቱና ገለልተኛነቱ የሚታመንበት፤

**ርዕሰ-ጉዳዮች፡** በሃገር አቀፍ ደረጃ አስፈላጊና ተገቢ የሆኑ፤ በወቅቱ ሃገሪቱን ለአጅግ ፈታኝ ሁኔታ የዳረጉ፤ ነገር ግን ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ጉዳዮች፤

**አቅም-ግንባታ፡** ውስጣዊ አካላትን እና አደራዳሪዎችን በአገራዊ ምክክር ንድፍ፤ ሂደቱን በማዘጋጀትና በድርድር ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችንና አቅም ግንባታ በማዘጋጀት ቴክኒካዊ ብቃታቸውንክህሎታቸውን ማጎልበት፤

**የሃይል ሚዛን፡** በምክክር መድረኩ ለሚያጋጥሙ የሃይል የበላይነትና ሽኩቻ የሚስተናገድበትን ስርዓት ማበጀት፤ በምክክርና ድርድር አነስተኛ ልምድ ያላቸው ባለድርሻ አካላት የመደራደር አቅማቸውን ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታ መርሃ-ግብር ማዘጋጀትና ማብቃት፤



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra
Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA
swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation

በመሆኑም በውጭ ድጋፍ ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ማናቸውም ጉዳዮች ራሳቸውን ችለው ለማከናወን የመተማመን መንፈሳቸውን ያሳድጋል፤

**ቅድመ-ዳሰሳ እና ዝግጅት፡** የአገራዊ ምክክር ሃሳብን በህዝቡ እና በፖለቲከኞች በመሳሰሉት በማስተዋወቅ፤ በማስረጽ፤ የግጭት ተዋንያንን ከወዲሁ ማዘጋጀት፤ አለም-አቀፋዊ ወይም ክልላዊ ቁርጠኝነት እና ፈንዶችን ማፈላለግ፤  እና የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂዎችን መንደፍ፤

**ትግበራ፡** ስምምነት የተደረሰባቸው ውጤቶችን ወደ ተግባር የማሸጋገር፣ ተዋዋይ ወገኖችን ለስምምነቱተገዥ/ተጠያቂ የሚያደርግ ስልጣን ማግኘት፤

ከአለም-አቀፍ ማኅበረሰብ ለትግበራው የሚያስፈልጉ ፈንዶችን፤ ሙያዊ እገዛ፣ እና አግባብነት ያላቸውን ማዕቀቦች ለመጣል ድጋፎችን ማግኘት፤

**የደህንነት ዋስትና፡** ያለ ፖለቲካዊ ጫና ስጋት በነፃነትና እና ሙሉ ኃላፊነት ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ምህዳር መፍጠር፤ በሂደት ላይ ያሉ ግጭቶችን ማስቆም፤ ተቃዋሚ ቡድኖችን አለማገድ፣ የሚዲያ ነፃነትን ማረጋገጥ።

**የሽግግር ፍኖተ-ካርታ፡** ተዛማጅ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፤ መዋቅራዊ እና የፍትህ ሪፎርም ሂደቶችን፤ የአጭር ጊዜ ሰብአዊ ቀውስ ማገገሚያ እርምጃዎች እና የኢኮኖሚ ማነቃቂያ  መርሃ-ግብሮችን እንደ ሰላም ዋስትና ማድረግ፤

# አከራካሪ፤ አወዛጋቢ እና አሻሚ ጥያቄዎች

አገራዊ ምክክሮች ውስብስብ እና ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቁ ሂደቶች ናቸው። በዋናነት ፖለቲካዊ ባህሪ ያላቸው፤ የፖለቲካ ሽኩቻን የሚጋብዙ፤ በጠባብ ግላዊ ፍላጎቶች እና/ወይም በፓርቲ ፖለቲካዊ እቋሞች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ክልላዊ እና አለም--አቀፋዊ ተዋንያንም እንዲሁ በአገራዊ ምክክር ሂደቱ ከሚኖራቸው የደጋፊነት፣ አያገባኝም ባይነት ወይም አደናቃፊነት ሚናዎች አማራጮች የትኛውንም ቢከተሉ ተመሳሳይ ሁኔታ ይስተዋላል። በተጨማሪም በየትኛውም አካባቢ የሚገኙ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች እና ሲቪል ማኅበራትም እጅግ በርካታ አገራዊ ምክክሮች ተጨባጭ ውጤቶችን ሳያስገኙ የመከኑበትን አጋጣሚዎች በመጠቆም ያላቸውን ስጋት ይገልፃሉ፡፡ በዚህም የተነሳ እውነተኛ ምክክር የመካሄዱ እጣ ፈንታ እንዲሁም በሃቀኛነት መተግበሩ ላይ ተስፋ ማጣትን ያስከተለ በመሆኑ፤ ጥርጣሬን እና የምክክር መሰላቸትም አስከትሏል። አገራዊ ምክክሮችም ሆኑ የትኛውም የድርድር ሂደት አብዛኛውን ጊዜ ግጭትን በሌላ ዘዴ ማስቀጠያ ተደርገው ይወሰዳሉ። እንዲሁም አገራዊም ሆነ ምክክራዊ ያልሆኑ እና በሃሳብ ደረጃም ቢሆን ጉድለት የሚታይባቸው ስልቶች ተድርገው ይታያሉ። ምንም አንኳን በ'መመሪያ መፅሃፍ ደረጃ የሚዘጋጅ ቢሆንም፤ በተግባር ግን ሂደቱን ከሚያከናውኑ ወይም ከሚደግፉ አካላት ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ወደ መምከን ያመራል፣ ለምሳሌ ክልላዊ ሃይሎች ጣልቃ ሲገቡ፣ አለም-አቀፍ ሃያላን ድጋፋቸውን ሲያቋርጡ ወይም ሃገሩ በሶስተኛ ወገን ወደ ጦርነት ሲገባ ሊሆን ይችላል፡፡

የግጭት አካላት እንዲሁም  ባለሙያዎች እና ለጋሾችም ይህ ክስተት በየትኛውም ደረጃ ሊያጋጥም እንደሚችል በመገንዘብ በሃቀኝነት የራሳቸውን ግምገማ በማከናወን በዚያ አውድ ውስጥ በተጨባጭ የሚሆነውን መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ ሂደቶች አብዛኛውን ጊዜ *በአስፈላጊነት* (በነባራዊ ሁኔታው ውስጥ ምን ሊከሰት እንደሚችል)፣ *በሚፈለገው* (በሃሳብ ደረጃ የትኛው እንደሚቻል) እና *የሚኖሩ እድሎች* (የትኛው እንደሚሻል) መካከል የመዋዘቅ አዝማሚያን ያመላክታሉ። በተጨማሪም አገራዊ ምክክር አስፈላጊ የሚሆነው የህዝብና የመንግስት ግንኙነቶች ሲስተጓጎሉ እና ሲሻከሩ በመሆኑ፤ ይህንን መልሶ ውጤታማ የምክክር ሂደትን ለመቅረጽና ለመተግበር እጅግ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በመንግስት፤ በተወካዮቹ እና ተቋሞቹ እምነትን እና በራስ መተማመንን ለማፅናት የረጅም ገዜ ሂደት የሚፈልግ በመሆኑ ከአገራዊ ምክክሩ ወቅት ባለፈ ዘለቄታዊነት አለው፡፡

ይህ መመሪያ መፅሃፍ የአገራዊ ምክክር ሂደቶችን ለመንደፍ እና ለመተግበር ቴክኒካዊ እርምጃዎችን እና አማራጮችን የሚጠቁም እንደመሆኑ፤ በዝግጅቱ ወቅት የእነዚህ ሁኔታዎች ተለዋዋጭነትና የፕሮጀክቱ ፖለቲካዊ ባህሪ እና የሚያስከትላቸው በርካታ መሰናክሎች ላይ ትክክለኛ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡ መሰናክሎችን ከሚያስከትሉት ጉዳዮች መካከል በውሳኔ-አሰጣጥ፣ የሃይል መመጣጠኖች፣ የባለሙያዎች ቴክኒካዊ አተገባበር ግድፈት፤ መመሪያውን የመሸራረፍና ፖለቲካዊ ይዘት የመስጠት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን፤ በዚህ መመሪያ መፅሃፍ በቂ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል ተብሎ አይገመትም፡፡ የመመሪያ መፅሃፉን የተሟላ ከማድረግ አንፃር ቀሪ ሥራዎች እንዳሉት፤ ስለሆነም ቀጣይ ሙያዊ ክርክሮችን የሚጋብዝና ታዳጊ የጥናትና ምርምር መስክ በመሆኑ ሙያውን የበለጠ ለማዳበር የሚያነሳሳ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ
ውጭ ጉዳይ ቢሮ

Berghof Foundation

# ስለ አገራዊ ምክክር መመሪያ መፅሃፍ

የመመሪያ መፅሃፉ በሁለት-አመት የፕሮጀክት ማዕቀፍ (እ.ኤ.አ መጋቢት 2015 – ሚያዚያ 2017) የቤርግሆፍ ፋውንዴሽን ከስዊስፒስ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ፈንድ በጀርመን ፌዴራል ውጭ ጉዳይ ቢሮ ከስዊስ ፌደራል ውጭ ጉዳይ መምሪያ ጋር በመተባበር የተደገፈ ነው። የመመሪያ መጽሀፉ በአዲስና አሳታፊ በሆነ የጥናት አቀራረብ፣ በአገራዊ ምክከሮች በቀጥተኛ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላትና ባለሙያዎች ተሞክሮዎችን በቀዳሚነት በማጣቀስ የዳበረ ነው። የቤርግሆፍ ፋውንዴሽንም ከስዊስፒስ ጋር በመተባበር ለተለያዩ አገራዊ ምክከሮች እና የሽግግር ሂደቶች ድጋፎችን በመስጠት በርካታ ስልቶችን በመተግበር ያካበቷቸውን ጥልቅ ልምዶችን  በማጠናቀር ተጠቅሟል፡፡ ይህም የጓቲማላ፣ ሊባኖስ፣ ሊቢያ፣ ማሊ፣ ኔፓል፣ ሱዳን እና ቱኒዝያ ዝርዝር የትግበራ ጥናቶችን የሚያካትት ሲሆን፤ ሪፖርቶቹ የተዘጋጁት በሂደቶቹ በቀጥታ ከተሳተፉ የአካባቢው ባለሙያዎች እና ውስጣዊ ቡድኖች በተውጣጡ የባለሙያዎች ቡድኖች ነው፡፡ ዝርዝር የትግበራ ጥናቶቹን የበለጠ ለማዳበር ከጭብጣዊ ጥናቶች፤ የተለያዩ አካባቢዎች አገራዊ ምክክሮችና ተመሳሳይ ሂደቶች ሁሉን-አቀፍ የዳሰሳ ጥናቶች፣ በባለሙያዎች የነቃ ተሳትፎ ከተካሄዱ በአገራዊ ምክክሮች ላይ ውይይቶች እና የፕሮጀክቱ አማካሪ ቡድን ምክረ ሃሳቦች ጋር ለማጣጣም ጥረት ተደርጓል። የአማካሪ ቡድኑ አካል በመሆን አለም-አቀፋ ባለሙያዎች፣ ቴክኒካዊ ቡድኖች እና የተመድ ልዩ አማካሪዎችም እንዲሳተፉ በመደረጉ በመመሪያ መፅሃፉ ይዘት ላይ ጥልቅ እይታቸውን እንዲያቀርቡ እና በተግባር ላይ ለሚያጋጥሙ ችግሮች/ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሾች እንደሚሰጡ ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡

**በዚህ ፕሮጀክት አውድ የተካተቱ ሁሉም ህትመቶች በሚከተለው ማግኘት ይቻላል፡ www.berghof-foundation.org/publications/national-dialogue-handbook.**



Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

Eidgenössisches Departement für auswärtige Angelegenheiten EDA

swisspeace
Schweizerische Friedensstiftung
Fondation suisse pour la paix
Fondazione svizzera per la pace
Swiss Peace Foundation